የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

| ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፷፬<br>አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም | በአዲስ አበባ ከተማ<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 31th Year No. 64<br>ADDIS ABABA, this December 24th, 2022 |
|---|---|---|

<u>ማውጫ</u>

**<u>ደንብ ቁጥር ፻፶፬/፪ሺ፲፭</u>**

**<u>የአዲስ አበባ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ</u>**

**ገፅ----------------------------- ፫ሺ፪**

**<u>CONTENT</u>**

**<u>REGULATION NUMBER 154/2023</u>**

**<u>A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ADDIS ABABA LIGHT RAIL TRANSPORT SERVICE ENTERPRISE</u>**

**Page ---------------------------- 3002**

## <u>ደንብ ቁጥር ፻፶፬/፪ሺ፲፭</u>

## <u>የአዲስ አበባ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገትን ለማሳካት ቀልጣፋና ተደራሽ የብዙሃን ትራንስፓርት አገልግሎት ሰጪ ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቀናጀ የብዙሃን ትራንስፓርት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት በማቋቋምና የተቋሙን አደረጃጀት ለመወሰን ለከተማው ኅብረተሰብ የተሻለና ውጤታማ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## <u>REGULATION NUMBER 154/2023</u>

## <u>A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ADDIS ABABA LIGHT RAIL TRANSPORT SERVICE ENTERPRISE</u>

**WHEREAS,** it has been found necessary to establish an efficient and accessible mass transport providing institution to fulfil the fast economic and social development of the city of Addis Ababa;

**WHEREAS,** it has been found necessary to establish an enterprise that provides an integrated mass transportation service in the Addis Ababa city government and determine the organization of the thereof to provide a better and effective mass transportation service to the residents of the city;

.

ያንዱ ዋጋ..........
Unit price..........

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፶፭ሺ፮፻፺፰
Addis Negari Gazeta P.O.Box 55698

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሠን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፸፬/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፷፭ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና አንቀጽ ፺ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፶፬/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪. **"ደንብ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን እና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፺፩ ነው፤

፫. **"ቦርድ"** ማለት በደንቡ መሠረት የሚቋቋም የድርጅቱ የሥልጣን አካል ነው፤

፬. **"ባቡር"** ማለት የራሱን የሞተር ኃይል በመጠቀም ወይም በሌላ የሞተር ኃይል በተገጠመለት ተሽከርካሪ በመሳብ ወይም በመገፋት በሃዲድ ላይ የሚጓዝ ተሽከርካሪ ሲሆን ሎኮሞቲቭ ወይም ፉርጎ በመባል የሚከፈል ነው፤

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Sub-Article (5) of Article 65 and Article 90 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 74/2021, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## <u>PART ONE</u>
## <u>GENERAL PROVISIONS</u>

**1. <u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as: **"The Addis Ababa City Light Rail Transport Service Enterprise Establishment Regulation Number 154/2023."**

**2. <u>Definition</u>**

In this Regulation:

1. **"Government"** means the Addis Ababa city government;
2. **"Regulation"** means Regulation number 14/1999 that determines the administration and establishment of the Addis Ababa city government public enterprises;
3. **"Board"** means a governing body which is established according to the Regulation;
4. **"Train"** means a vehicle that moves on a railroad with its own engine or through a pull or push of another vehicle with an engine and it is divided with locomotives or wagons.

## ክፍል ሁለት

## ስለድርጅቱ መቋቋምና ዓላማ

### ፫. መቋቋም

፩. የአዲስ አበባ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት (”ከዚህ በኋላ “ድርጅት” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የድርጅቱ ተጠሪነት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፓርት ቢሮ ይሆናል፤

፫. ድርጅቱ በደንቡ መሠረት ይተዳደራል፡፡

### ፬. ዓላማዎች

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩. በቴክኖሎጂ በተደገፈ የከተማ ባቡርን በመጠቀም በተመጣጣኝ ዋጋ፣ ምቹ፣ ቀልጣፋ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ያልተቆራረጠ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

፪. የባቡር እና የባቡር መሰረተ ልማትን ጥራት ያለው ጥገና እና እድሳት አገልግሎት መስጠት፤

፫. የባቡር እና የባቡር መሰረተ ልማት አውታሮችን ደህንነት ማስጠበቅ፤

፬. በከተማው ውስጥ የባቡር መሰረተ ልማት አውታሮችን መገንባት እና ለነዋሪው ተደራሽ ማድረግ፤

፭. ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ተማሪዎች፣ አቅመ ደካሞች እና ነፍሰጡር ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ምቹና አስተማማኝ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

## PART TWO

## ESTABLISHMENT AND OBJECTIVE OF THE ENTERPRISE

### 3. Establishment

1. The Addis Ababa light Rail Transport service enterprise (hereinafter referred to as the **“Enterprise”**) is hereby established as public enterprise of the Addis Ababa City Government having its own legal personality;
2. The enterprise shall be accountable to the Addis Ababa city government transport bureau;
3. The Enterprise shall be governed according to the Regulation.

### 4. Objectives

The objectives for the establishment of the enterprise are the following:

1. Provide an affordable, convenient, efficient, safe, and uninterrupted transport service using technology assisted urban trains;
2. Provide quality maintenance and renovation services for trains and train infrastructures;
3. Protect the safety of train and train infrastructures;
4. Carry out the construction of train infrastructures in the city and make it accessible for residents;
5. Provide a convenient and reliable train service using modern technology that benefit students, incapacitated individuals, and pregnant women;

፮. በባቡር መሰረት ልማት ኮሪደር ላይ የሚገኙ ቦታዎችን በማልማት ለማስታወቂያና ሌሎች አገልግሎቶች በማዋል ተጨማሪ ገቢ ማስገኘት፤

፯. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሌሎች ተዛማጅ ስራዎችን ማከናወን፡፡

**፭. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮ የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

**፮. ዋና መሥሪያ ቤት**

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በከተማው ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

**፯. ካፒታል**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፴ ቢሊዮን ፪፻፸፪ ሚሊዮን ፰፻፴፭ ሺ ፭፻፸፫ (ሰላሳ ቢልዮን ሁለት መቶ ሰባ ሁለት ሚልዮን ስምንት መቶ ሰላሳ አምስት ሺ አምስት መቶ ሰባ ሶስት ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ፳፭ ቢልዮን ፶፱ ሚሊዮን ፪፻፳፬ ሺ ፫፻፶፭ ብር (ሃያ አምስት ቢልዮን ሃምሳ ዘጠኝ ሚልዮን ሶስት መቶ ሃምሳ አምስት ሺ ብር) በዓይነት እና ፩ ቢሊዮን (አንድ ቢሊዮን በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

6. Generate additional income through developing areas located around the train infrastructure corridor and using them for advertisement and other services;
7. Carry out other related activities that help to attain its objectives.

**5. Regulatory Authority**

The Addis Ababa city government finance bureau shall be the regulatory organ of the enterprise.

**6. Head Office**

The head office of the enterprise shall be in Addis Ababa city and it may have branch offices in different areas of the city as may be necessary.

**7. Capital**

The authorized capital for the Enterprise is birr 30,272,835,573 (thirty billion, two hundred seventy two million, eight hundred thirty five thousand, five hundred seventy three birr) and from this birr 25,059,224,355.00 (twenty five billion, fifty nine million, two hundred twenty four thousand, three hundred fifty five birr) is paid up in kind and 1,000,000,000 (one billion birr) in cash.

፰. <u>**የኃላፊነት ወሰን**</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፱. <u>**ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**</u>

ድርጅቱ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፡፡

፲. <u>**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ ከታህሳስ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፭ዓ/ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

8. <u>**Liability**</u>

The enterprise shall not be held liable beyond its total asset.

9. <u>**Effective Period of the Enterprise**</u>

The enterprise shall exist for an indefinite period of time.

10. <u>**Effective Date**</u>

This Regulation shall enter into force as of December 24/ 2023.

**Done at Addis Ababa, this –December 24 2023.**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**